
ሀብ ረተሰብ ሳይንስ
6ኛ ክፍል

ኑር አፍሪካ አካዳሚ



የክለሳ ማስተዋሻ

አዘጋጅ : አብዱ አሊ

ጥቅምት 2013

ምዕራፍ አራት

ህዝባዊ ጉዳዮች

የሥነ ህዝብ ጉዳዮች

- ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስን ለመዋጋት የማህበረሰቡ አጋርነት ና የዜግነት ድርሻን መወጣት
- የምጣኔ ሀብት ና የማህበራዊ ችግሮች መንስኤ ነው።
- የተማሩና ሙያ ያላቸዉን ሰዎች ህወት ያጠፋል።
- ህፃናትን ያላሳዳጊ ና አረጋውያንን የለጧሪ ቀባሪ ያስቀራል።
- ይህ ሁኔታ ደግሞ የሀገርን እድገት ይገታል።

ኤች አይ ቪ ወይም ኤድስን ለመዋጋት ጠቃሚ ዘዴዎች

- ልቅ የሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነት አለማድረግ
- ስለታም ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም
- በበሽታው ለተያዙ ሰዎች ሳያገሉ እንክብካቤ ማድረግ

እንክብካቤ ና ድጋፍ መስጠት

- የኤች አይ ቪ ወይም ኤድስ በሽታ በደማቸው ያለባቸውን ወገኖች አለማግለልና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ነው።
- ወላጆቻቸዉን ያጡ ህፃናትን ተገቢውን እንክብካቤ በማድርግ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠትና አለኝታነትን በተለያዩ መንገድ በመግለፅ ከጎናቸው መቆም ወዘተ ናቸው።

ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት

- ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት ማለት በአንድ ሀገር የህዝብ ቁጥር መጨመር ማለት ነው።

ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት ውጤቶች


- የምግብ እጥረት
- የልዩ ልዩ በሽታዎች መከሰት
- የመኖሪያ ና የእርሻ ቦታ እጥረት
- የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ

ለህዝብ ቁጥር መጨመር መፍትሔዎች

- የአንድን ሀገር ምጣኔ ሀብት የህዝቡን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችልበት ደረጃ ማሳደግ ነው።
- የህዝብ ቁጥር እድገትን ህዝብን በማስተማር መገደብ ወዘተ...ናቸው።

የህፃናት መብቶችና አያያዝ

- የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መብቶች አዋጅ መሠረተ ሀሳብ
- እያንዳንዱ ዜጋ የተሻለ ህብረተሰብና ሀገር ለማየት የሚከተሉትን ጠቃሚ ነገሮች ማድረግ ይኖሩበታል።
- እነሱም፥ የህፃናትን መብት ማስከበር
- የህፃናት ደህንነት መጠበቁን ማረጋገጥ
- ህፃናት ግዴታቸዉንና ሀላፊነታቸዉን መወጣት



የህፃናት መብቶች ማስከበሪያ ስልቶች

- በህፃናት ላይ የሚፈፀም የመብት ጥሰት ለማስወገድ ዜጎች ንቁ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል።
- የህፃናትን መብት ጥሰት ለመከላከል ስለመብት ጥሰት ምንነት ግንዛቤ ማስጨበጥ እንዲሁም ከአደጋ እንዴት ማምለጥ እንደሚችሉ ማስገንዘብ ጠቃሚ ነው።
- ህፃናት በህግ የተሰጣቸው መብት በግለሰብ ፣ በቡድኖች ወይም በድርጅቶች ሊገሰስ፣ አካላዊ፣ስሜታዊና ስነልቦናዊ ጫና በማድረስ ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባራት ሲፈፀሙ የመብት ጥሰት ተፈፀመ ይባላል።

የህፃናት መብት ጥሰት መንስኤዎች

- የምጣኔ ሀብት እድገት ጎላቀርነት
- ማህበራዊ እድገት ጎላቀርነት

የምጣኔ ሀብት እድገት ጎላቀርነት

- ከባድ የጉልበት ስራ ማሰራት
- በመያዣነት በመስጠት ገንዘብ መበደርና መሸጥ
- በወሲብ ንግድ በማሰማራት፣በልመና ተግባር ላይ ማዋል ናቸው።
- **የማህበራዊ እድገት ጎላቀርነትም** ሌላው የህፃናት መብት ጥሰት መንስኤ ነው።
- ለምሳሌ፦ ከባድ አካላዊ ቅጣት
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ የአካል ጉዳትና የመንፈስ ጉዳት ያደርሳል። ይህም ደግሞ ህፃናቱ የበታችነት ስሜት እዲሰማቻው፣ በራሳቸው የመተማመን ብቃት እንዳይኖራቸውና በትምህርታቸው ጠንክረው ለስኬት እንዳይበቁ ያደርጋል።

ግዴታንና ሀለፊነትን መወጣት

- መብት አንድ ሰው ነሀላፊት ነው።
- ለአደጋ የሚያጋልጡ ተግባራትና መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች
- አደጋ የሚያስከትሉ ተግባራትና የደህንነት እርምጃ አወሳሰድ
- ዘመናዊ የኑሮ ሁኔታዎችን የሚመራባቸውን በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይጠቅማል። የቴክኖሎጂ ውጤቶች ስራን በቀላሉ ለ ቅማሉ። ህይወት ለሰዎች እንዲሆን ያደርጋል። የቴክኖሎጂ ውጤቶች በጥንቃቄ ካልተያዙ አደገኞች ናቸው። ህይወትንና ንብረት ሊያጠፉ ይችላሉ።
- ኮረንቲ ብርሀን ለመስጠት፣ሙቀት ለማገኘትና ሞተሮችን ለማንቀሳቀስ ይጠቅማል።
- መርዝ፦ አደገኛ የሆነ ሰው ሰራሽ ነገር ነው።መርዝ ከተዋጠ ወይም ከሰውነት ጋር ከተዋህደ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከትል ነገር ነው።መርዞች ኬሚካሎች ሆነው በጠጣር፣በፈሳሽ ወይም ወይም በጋዝ መልክ ይገኛሉ።
- እሳት፦ መቀትናጉልበት ሰጪ ክስተት ነው። እስት በጥንቃቄ ካልተያዘ አደገኛ ነው። ቤንዚን፣ ነጭ ጋዝና ደረቅ እንጨት በቀላሉ የሚቀጣጠሉ ስለሆነ ከእሳት አጠገብ ማስቀመጥ ወይም በአካባቢው የክብሪት ወይም የሲጋራ ቁራጭ መጣል አይገባም።
- ፈንጂዎች፦ የሚፈነዱ ነገሮች ሰው ሰራሽ ሲሆኑ በአጠቃላይ ፈንጂዎች በመባል ይታወቃሉ። ፈንጂዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው። ጦርነቶች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች አደጋ ለማድርስ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

የአጋ ርነት ጉዳዮች

ክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች

- በሀገራት፣ በክፍለ አህጉራት፣ በአህጉራትና በዓለም ደረጃ የሚደረግ የትብብርና የስምምነት ውል አጋርነት ይባላል።
- የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የአጋርነት መርሐ ግብር
- የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ድንበር፣ የህዝብ እንቅስቃሴ፣ ተመሳሳይ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት፣ ተመሳሳይ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ተመሳሳይ የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት አሏቸው።
- የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት***(Intergovernmental Authority on Development)IGAD***
- ይህ ድርጅት የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ1986ዓ ም ነበር። የተቋቋመው ክልሎቹ ከፍተኛ ድርቅ ባጋጠማቸው ወቅት ነበር። ዓላማውም ድርቅ ያስከተለውን ችግር ለመቋቋም ነበር።
- ድርጅቱ በአባል ሀገራቱ መካከል ትብብርን በማጠናከር በክልሉ፦
- የምግብ ዋስትናና የአካባቢን ጥበቃን የማረጋገጥ
- ሰላም፣ጸጥታና ሰብዓዊ ጉዳዮችን የመጠበቅ
- ምጣኔ ሀብታዊ ትብብርንና ውህደት የመፍጠር ተልዕኮ ይዞ ይንቀሳቀሳል።

የናይል ተፋሰስ ኢንሸቲቭ



- ናይል በዓለም ረጅሙ ነው። የወንዙ ተፋሰስ ስፋት ከሶስት ሚሊዬን ካሬ ማይሎች ይበልጣል።
- የናይልን ወንዝን ውሀ 86 ከመቶ የምታቀርበው ኢትዮጵያ ናት፣የቀሩት ሀገር ድርሻ 14 ከመቶ ብቻ ነው።
- የተፋሰሱ ጠቅላላ ስፋት በአስራ አንድ የተፋሰሱ አገሮች መካከል የተከፋፈለ ነው።።
- እነሱም፦ኢትዮጵያ፣ ቡሩንዲ፣ ኤርትራ፣ ዩጋንዳ፣ታንዛኒያ፣ ሩዋንዳ፣ ኬንያ፣ደቡብ ሱዳን፣ ሰሜን ሱዳን፣ ግብፅና ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ናቸው።

የናይል ተፋሰስ የአጋርነት ግብ

- የናይል ወንዝ አጠቃቀም በፍትትሀዊ አጠቃቀም ላይ የተመሰረተ አይደለም። ግብፅ ከሁሉም በላይ በናይል ወንዝ ተጠቃሚ ስትሆን በሁለተኛ ደግሞ በሁለተኛ ደግሞ ሰሜን ሱዳን ናት።
- ከ1990ዓ ም ጀምሮ ይህን የተዛባ የውሀ አጠቃቀም ለመለወጥ ሙከራ ተደርጎ ነበር። ሙከራው የተጀመረው የናይል ተፋሰስ ኢንሸቲቭ በሚል ድርጅት ነበር። ድርጅቱ የኮረንቲ ሀይል አጠቃቀም፣ የውሀ ሀብት አጠቃቀም አግባብነትና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ በጋራ ፕሮጀክቶች እውን መሆን ላይ የሚሰራ ነው።

የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ

- የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ አምስት ሀገራት የያዘ ሲሆን እነሱም፦ የኬንያ ሪፐብሊክ፣ ዩጋንዳ፣ የተባበሩት የታንዛኒያ ሪፐብሊክ፣የሩዋንዳ ሪፐብሊክና የብሩንዲ ሪፐብሊክ ናቸው። መቀመጫው በታንዛኒያ አሩሻ በምትባል ከተማ ነው።
- የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ የአጋርነት ግብ በ1991ዓ.ም ተቋቋመ።
- የማህበረሰቡ ዓላማ የበለፀገ፣ተወዳዳሪ፣ ሰላማዊና የተረጋጋ፣ በፖለቲካ አስተዳደር የተዋሀደ ምስራቅ አፍሪካን መፍጠር ነው።